# ውሾቹ ተንጫጩ

ድኩማን ጀኔራል ፣ ያራተኛ ክፍሉ
ከዕውቀት የተፋታው ፣ አዛዥ ኮሎኔሉ
ስሙን አስተካክሎ ፣ የማይጽፈው ሁሉ
በተገዛ ዲግሪ ፣ አንቱ የሚባሉ
እሾህ አሜኬላ ፣ ዝቃጭ የተጣሉ
ዘረኝነት ብቻ ፣ ድሩም ማጉም ፈትሉ
የተማረን ጠላት ፣ አድርገው የማሉ
ልናይ ነው ዘንድሮ ...
የት እንደሚገቡ ፣ የት እንደሚውሉ ።

ህዝብን ማሰቃየት ፣ በመግደል በማፈን
ጥጋብ የወጠረው ፣ የተነፋ ወይፈን
በዘረፋ ዲናር ፣ በስርቆት መጀነን
ከበሮ መጎተት ፣ ሹሩባን መቆነን
ስካርና ዝሙት ፣ ጠኋት ማታ መዝፈን
ለድርቡሽ ወያኔ ፣ አብቅቷል ያዘመን ።

ጭንቅላቱ ባዶ ፣ አይምሮው ሆዳቸው
ሽጉጥ የታጠቀው ፣ ጳጳሱ ካድሬያቸው
አልሞ ተኳሹ ፣ ደም የሚያጠጣቸው
በቀበሌ ያለው ፣ ተናካሽ ውሻቸው
እበላ ባይ ሆዳም ፣ ተስፈኛ አንጋቻቸው
የምጥ ቀን ደረሰች ፣ ሞልታለች ጽዋቸው
መሬት ተሰንጥቃ ፣ መቼም አትውጣቸው
ሁሏም ይከፍሏታል ፣ እንደየስራቸው
የነ ሃጎስ ውሾች ፣ የት ይሆን መግቢያቸው ።

ያስተሳሰብ ደሃ ፣ በእምነት የቀጨጩ
ፍርደ ገምድል ዳኛው ፣ ፈላጩ ቆራጩ
አንዱን ጎሳ ካንዱ ፣ የኖሩ እያጋጩ
አጥንት የሚግጡ ፣ ስጋን የሚነጩ
ለማወራረጃ ፣ ደም የሚጎነጩ
ምድሪቷን ሕዝቡንም ፣ በደረቅ የላጩ
የሚቦጠቡጡት ፣ ደረቀና ምንጩ
የሃጎስ ቡችሎች ፣ ዝርክርክ ለሃጩ
ቡፍ ቡፍ አበዙ ፣ ውሾቹ ተንጫጩ
ደርሷል ልናያቸው ፣ በንባቸው ሊራጩ
የማያልፍ መከራ ፣ ሊከኩ ሊፈጩ ።

ታዛቢው

February 1, 2018